**ለቤተሰባዊ ተሳትፎ የሚመከሩ**

"እናቴ ላግዝሽ!"

ኖኒ የርኅራኄ ምልክቶችን ማሳየት በመጀመሩ የእናቱን ችግር ተረድቶ እርሷን ለመርዳት ያስባል። ታሪኩ የሕጻናቱን የእድገት ጉዞ እንድንከታተል፣ የሚያስፈልጋቸውን የነጻነት ጊዜዎች እንድንለይ፣ እርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ እንድንፈትንና በምን ዓይነት ተግባራት እራሳቸውን እንደሚረዱና ለሌሎች ሰዎች ችግር ያላቸውን ስሜት እንዴት እንደሚገልጹ እንድንረዳ ይጋብዘናል።

**ከታዳጊ ሕጻናት ጋር ለማንበብ ጠቃሚ ምክር**

እንደ ቤተሰብ ከማንበብዎ በፊት መጽሐፉን ብቻዎን ማንበብ አለብዎት። ከመጽሐፉ ጋር ቀድሞ መተዋወቁ በቅደም ተከተልና ለታዳጊ ህፃናት ተስማሚ በሆነ ፍጥነት ለማንበብ ይረዳል። ደስ የሚል ንባብ!

የQR ትርጉምና በላዩ ላይ ይፃፉ –አማርኛ /Pyc / Eng

**መነጋገር - ማን ሊያግዝ ይችላል?**

ሁሉም ሰው ሌሎችን ታዳጊ ሕጻናትን እንኳን ሳይቀር ሊያግዝ ይችላል። ታዳጊ ሕጻናቱን ሌሎችን በምን እንደሚያግዙ መጠየቅ ወይም በሚከሰትበት ጊዜ እንደሚረዷቸው መንገር ይችላሉ፦ "ጠረጴዛውን ለማዘጋጀት እንደረዳኸኝ አስታውስ?"፣ "መጫዎቻዎቹን ለማዘጋጀት እንዴት እንደረዳሽኝ ተመልከቺ!"

**ታሪኩን ማዳመጥ**

"ኖኒና እናቱ" የሚለውን ታሪክ ማዳመጥ ይፈልጋሉ? - የQR ኮዱን ስካን ያድርጉና የታሪኩ የድምጽ ቅጂ ላይ ይደርሳሉ። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ በሚጫወቱበት ወይም አብረው ተቀምጠው መጽሐፍ በሚያገላብጡበት ጊዜ ማዳመጥ ይችላሉ።

**ታሪኩ በምስል**

ስዕሎቹ የታሪኩ አካል ሲሆኑ በእነርሱ አማካኝነት ታዳጊ ሕጻናቱ የታሪኩን ሂደትና ዝርዝሮቹን ያውቃሉ፤ ያስታውሳሉም። ስዕላዊ መግለጫዎቹን አንድ ላይ በማየት ኖኒ ለእናቱ የሰጣትን ዕቃዎች መፈለግ ይቻላል። 'ቦርሳ የተሳለበት ቦታ የት ነው?' እና 'የኮት ምስል የት አለ?'

**ጨዋታ - የእቃዎች ግንብ**

በእናት ላይ በተቆለሉ ነገሮች በመጠቀም በተራ የእቃዎችን ግንብ መገንባት ይችላሉ፦ በጥንቃቄ አንዱን በሌላው ላይ በማድረግ ኩቦችን፣ መጫወቻዎችን፣ ኮፍያዎችን፣ ቦርሳዎችንና ማከል የሚፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ማስቀመጥ ይችላሉ።

የፈጠራ ስራዎችን፣ ዘፈኖችንና ሌሎችን ስራዎች በፒጃማ ቤተ-መጽሕፍት ፒንተረስት ላይ